በ1986 ዓ.ም. የመጀመሪያው የዕብራውያን ት/ቤት በሪሾን ለጽዮን ከተማ ተመሠረተ። በ1898 ዓ.ም. የመጀመሪያው የዕብራውያን መዋዕለ ሕጻናት ተከፈተ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከተማችን ሪሾን ለጽዮን በትምህርታዊ ተሐድሶ በመምራት ላይ ትገኛለች።

በዘንድሮው የትምህርት ዘመን ማለትም በአ"ሠ በከተማችን ውስጥ 42664 ተማሪዎች በመማር ላይ ናቸው።

- 7259 ልጆች በ246 መዋዕለ ሕጻናት ውስጥ ይማራሉ።
- 18587 ተማሪዎች በ49 የ1ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ ይማራሉ።
- 16818 ተማሪዎች በመለስተኛና ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ ይማራሉ።

ከሀ"ሠ ዓ.ም. የትምህርት ዘመን ጀምሮ የከተማችንን የትምህርት ሥርዓት መቀየር ጀመርን። ከአ"ሠ የትምህርት ዘመን ጀምሮ ነጻ የሆኑ መለስተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶችን ከከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ጋር በማዋሃድ ባለ6 ዓመት ት/ቤቶች ሥርዓትን ፈጠርን። ይህም ከ1ኛ እስከ 6ኛ ክፍል እና ከ7-12ኛ ክፍል ነው።

ይህ ፕሮግራማችን የትምህርት ሚኒስትሩንና የትምህርት ሚኒስቴር ዋና ሥራ አስኪያጅን ቡራኬና ምስጋና አግኝቷል። ፕሮግራማችን ወደፊት ፍሬያማ እንደሚሆንና በእስራኤል የትምህርት ሥርዓት ውስጥ ለሪሾን ለጽዮን ከተማ የዕውቅና ቦታ እንደሚያስጥ ሙሉ እምነታችን ነው።

ተልእኳችን ገና አላለቀም። አሁን የምንገኝበት ተለዋዋጭ ሁኔታ በሙሉ ዓቅማችን እንድንሠራ የሚያደርገን ብቻ ሳይሆን ከሚመለከታቸው አካላት ጋርም ተባብረን እንድንሠራም ያስገድደናል። እንደዚሁም ለሥራችን ስኬት የሚረዳ መዋቅር በሁሉም የዕድሜ ክልል ላሉ ተማሪዎች እንድንዘረጋ ያደርገናል።

ይህ በከተማችን ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎችን ውጤታማ ለማድረግ የሚረዳ የተሐድሶ ሂደት ሲሆን ለተለያዩ ፍላጐታቸው መፍትሔ የሚሰጥ ይመስለኛል።

የተማሪዎችን ውጤት ለማሻሻል ትምህርት በሚከብዳቸው ተማሪዎች ላይ የምናተኩር ሲሆን በት/ቤቱ መዋቅር ውስጥ ተዋህደው እንዲማሩም ጥረት እናደርጋለን። ይህ የትምህርት ሚኒስቴር አጠቃላይ ዓላማ የከተማችን ደግሞ ልዩ ዓላማ ነው።

ከዚህ በታች ዋና ዓላማዎቻችን ተዘርዝረዋል።

- ለሁሉም ተማሪ እኩል የመማር መብት ማስገኘት
- ብልጫ ያለው ውጤት እንዲገኝ መጣጣርና ይህንንም መንከባከብ
- የባህልና የብሔራዊ አባልነት ስሜት ትምህርት መስጠት

- የመቻቻልና የጠብ መከላከያ ትምህርት
- የኅብረተሰባዊ ተሳትፎና የንቁ ዜግነት ትምህርት
- የአካባቢ እንክብካቤ ትምህርት
- በከፍተኛ ቴክኖሎጂ የታገዘ የመማርና የማስተማር ሂደት
- የላቀ ውጤት ያላቸው መምህራንና የትምህርት ሠራተኞች ማሰማራት
- በትምህርቱ ሂደት ወላጆችን ማሳተፍ
- ቀልጣፋ አገልግሎት
- ቀልጣፋና ብልጫ ያለው አደረጃጀት
- ንጹሕ በሆነ ቦታና ምቹና ደኅንነት በተመላበት ሁኔታ የሚሰጥ ትምህርት
- ለትምህርታዊ ተቋሞች ፈጣንና ቀልጣፋ ቴክኒካዊና የንብረቶች አያያዝ አገልግሎት
- የቁጥጥር ሥርዓትና የአስተዳደራዊ ሥርዓት ክትትል ናቸው።

ከአክብሮት ጋር
አሪኤላ እስራኤሊ
የትምህርት አስተዳደር ዋና ኃላፊ